# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ሰመጉ

# 141ኛ ልዩ መግለጫ

## በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት
## የማንነት ጥያቄ በሚያነሱ ዜጎች ላይ
## የሚፈጸም ግድያ፣ ሕገወጥ እሥራት፣ አፍኖ መሠወር፣
## ማፈናቀልና ንብረት መንጠቅ በአስቸኳይ ይቁም!

ግንቦት 24 ቀን 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council

የምዝገባ ቁጥር 1146
www.hrco.org.et

## ሰመጉ

### ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ


አ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ማኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info@hrco.org

ድረ ገጽ: www.hrco.org

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ


### የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ


ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: monitoringcomplaints@hrco.org


### ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

| | | |
|---|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና | - ሐዋሳ፡ | ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና | - ባሕርዳር፡ | ስ.ቁ (+251) 058 226-3913፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና | - ነቀምቴ፡ | ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና | - ድሬደዋ፡ | ስ.ቁ (+251) 025 811 9150 ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና | - ጅማ፡ | ስ.ቁ (+251) 147 211 5434 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና | - አዲስ አበባ፡ | ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432 |

# ማውጫ


1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ -------------- ------------------ 1
2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ -------------------------------- -------------------------- 2
3. መግቢያ ------------------------------ ---------------------------------------------- 3

ሀ. ከወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ
የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች--------------------------------------------------- 3

1. መንደርደሪያ -------------------------------------------------------------- 3
መልክዓ ምድር፣ አዋሳኞች፣ ባህልናቋንቋ፣ ኢኮኖሚ- ሐገራዊ አስተዋጽዖ --------- 3-4
1.1 በምርመራው ሥራ የተሸፈኑ አካባቢዎች -------------------------- 6
1.2 የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች ---------------------------- 6
1.3 በምርመራ ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ------------------------------ 7
2. የማንነት ጥያቄ በማንሳት ምክንያት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ..... 7
2.1 ሕገ ወጥ ግድያ --------------------------- ---------------------------------- 7
2.2. ታፍነው ተወስደው የደረሱበት የማይታወቅ ---------------------------------- 8
2.3. ድብደባና ማሠቃየት--------------------------------------------------------- 10
2.4 ሕገ ወጥ እሥራት-------------------------------------------------------------- 10
2.5 የእርሻ መሬት፣ መኖሪያ ቤትና ንብረት ነጠቃ----------------------------------- 11
2.6 መሣሪያቸውን የተነጠቁ አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች------------------------- 13
2.7 የተፈናቀሉ ዜጎች---------------------------------------------------------------- 13
2.8 የአካባቢና የቦታ ሥያሜ ለውጥ ----------------------------------------------- 14

ለ. የቅማንት ሕዝብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ
መብት ጥሰት ------------------------------------------------------------------- 16
1. መግቢያ -------------------------------------------------------------------------- 16
2. ሕገወጥ ግድያ ----------------------------------------------------------------- 17
3. በግጭቱ ወቅት የቆሰሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ------------------------------------ 18

ሐ. የቁጫ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ
መብት ጥሰት ------------------------------------------------------------------- 20


መ. የኮንቶማ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ
መብት ጥሰት ------------------------------------------------------------------- 20

4. ማጠቃለያ ----------------------------------------------------------------------- 21
5. ማሳሰቢያ ------------------------------------------------------------------------ 21

አድራሻዎች ------ ------------------------------ --------------------------------- 22-23


የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




---

የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

[1] "ኢትዮጵያ" [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)፣ የአሁኑ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም. በአባላት የተመሠረተ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው። ሰመጉ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት "ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር" ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው። ሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማህበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው።

ሰመጉ ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት ላለፉት 24 ዓመታት ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። ከነዚህም መካከል አንዱ ለሕዝብና በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው። የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል።

የሰመጉ መለያውና ግንባር  ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል።

በተጨማሪም በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ መስጠት፣ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወንና የአድቮኬሲ ሥራዎችን መሥራት፣ በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎች ይዘትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተልና የፍርድ ቤቶችን ሂደት መከታተል የሰመጉ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 140 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ሰመጉ አሁን በሚገኝበት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

### መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በሕገመንግሥት እውቅና ያገኙ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች በተለያዩ ምክንያቶች እየተጣሱ ይገኛሉ። አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ከፀደቀበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ከተነሱ የብሔረሰብ ማንነት ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች ለዚህ እንደማሳያ ሊጠቀሱ ይችላሉ። የወልቃይት ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የቅማንት ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የቁጫ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የኮንቶማ ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የወለኔ ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የዶርዜ ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄ፣ የስልጤ ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄና ሌሎችንም መሰል ጥያቄዎች ተከትሎ በርካታና የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ ከነዚህ መካከል የስልጤ ማሕበረሰብ ጥያቄ ብቻ መልስ ሲያገኝ ሌሎቹ ግን ወይ በከፊል ብቻ አለያም ሙሉ በሙሉ ምላሽ አላገኙም፡፡ በነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ሂደት ውስጥ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በጣም አሳሳቢ ነበሩ አሁንም ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በዚህ 141ኛ ልዩ መግለጫው፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ የወልቃይት ማሕበረሰብ አባላት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚኖሩ የቅማንት ማሕበረሰብ አባላትና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ የቁጫና የኮንቶማ ማሕበረሰቦች አባላት ያነሷቸውን የማንነት ጥያቄዎች ተከትሎ በተከሰተ ግጭት የደረሰውን የህይወት መጥፋት፣ የአካል መጉደል፣ ህገወጥ እስራት፣ የንብረት ውድመትና የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶችን በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

## ሀ. ከወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

### 1.1 *መንደርደሪያ*

የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ማንነት ጥያቄውን በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ አካላት ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ አሁንም በቅርቡ ቁጥራቸው 2253 የሆነ የወልቃይት ማሕበረሰብ አባላት በፊርማቸው አረጋግጠው ለ88 የኮሚቴ አባላት በሰጡት ሕጋዊ ውክልና መሠረት፣ እነዚሁ ተወካዮቻቸው በጥር 25 / 2008 ዓ.ም. በተጻፈና ሁሉም ፊርማቸውን ባሰፈሩበት ደብዳቤ ለሰመጉ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይህንንም አቤቱታቸውን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ለሚኒስትሮች ምክርቤት፣ ለኢፌዴሪ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ለፍትሕ ሚኒስቴር፣ ለኢሕአዴግ ጽ/ቤት፣ ለኢፌዴሪ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምና ለኢፌዴሪ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አቅርበዋል፡፡

የወልቃይት ማኅበረሰብ አባላት፣ የሐገር ሽማግሌዎችና ተወካዮች፣ ዛሬ የሚገኙበትን ነባራዊ ኹኔታና የማንነት ጥያቄ ለማንሣት ያስገደዷቸውን የሕገ መንግሥት ጥሰቶች፣ ከታሪክ፣ ከመልክአምድር አቀማመጥ፣ ከባሕልና ቋንቋ እንዲሁም ከኢኮኖሚ አንጻር እንደሚከተለው ይተነትናሉ፡

‹‹የወልቃይት ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልሕና አኩሪ ድርሻ ያለው ሲሆን ከአያት ቅድመ አያቶች ዘመናት ጀምሮ ታሪካዊ ማንነቱና ትውልዳዊ ዕርስቱ ታውቆና ቴክብሮ የኖረ ሕዝብ ነው …” በማለት ስለአካባቢው መልክዐምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለማህበረሰቡ ባሕልና ቋንቋና ሐገራዊ አስተዋጽዖ፣ ለሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች መርማሪ ባለሙያዎች በዝርዝር ያስረዱት በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### የወልቃይት መልክዐ ምድር

“ወልቃይት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሰሜን በጌምድር ጠቅላይ ግዛት በወገራ አውራጃ፣ በወታደራዊው የደርግ ሥርዓት በጎንደር ክፍለ ሐገር በወገራ አውራጃ ውስጥ የሚገኝ ወረዳ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከእኛ ከሕዝቡ ፍላጎትና ፈቃድ ውጭ ማንነታችን በማይገለጽበት በምዕራብ ትግራይ ዞን ተጠቃሎ ይገኛል፡፡ እኛ ግን ከአማራ ሕዝብ ጋር በታሪክ፣ በባሕል፣ በሥነ ልቦና እንዲሁም በመልክዐ ምድር ተሣሥረን የኖርን፤ አሁንም የተሣሠርን ሕዝቦች ነን›› በማለት የወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ለሰመጉ በጽሁፍ አስረድተዋል፡፡ …

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council *

### የወልቃይት አዋሳኞች

| | |
|---|---|
| በሰሜን፡ | የተከዜ ወንዝ/ኤርትራ |
| በደቡብ፡ | ጠገዴ |
| በምሥራቅ፡ | የተከዜ ወንዝ/ትግራይ |
| በምዕራብ፡ | አርማጭሆና ሱዳን ናቸው። |

### ባሕልና ቋንቋ

"የወልቃይት ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አማራ ሲሆን፣ የራሱ የሆነ የአማርኛ ቋንቋ ዘይቤ አለው፤ በተጨማሪም የድንበርተኛ ቋንቋዎች ማለትም ትግርኛና አልፎ አልፎም ከሱዳን በሚዋሰኑ አካባቢዎች የሱዳን ዐረብኛ ይናገራል። ባሕላዊ ዘፈኑ፣ ጭፈራውና ዳንኪራው፣ የኃዘን እንጉርጉሮው፣ ቀረርቶውና ሽለላው፣ ሃይማኖታዊ ሥነሥርዓቱ እንዲሁም ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ሳይቀር በአማርኛ ይከናወናሉ፤ የወልቃይት ማኅበረሰብ የሚናገረው ትግርኛም ከኤርትራና ከትግራይ ድንበሮች እየራቀ በሄደ ቁጥር እየደበዘዘ ይጌዳል። የወልቃይትን ማኅበረሰብ ከትግራይ ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖር ትግርኛ መናገሩ ሲሆን፣ እንደዚያም ሆኖ የወልቃይት ትግርኛና የትግራይ ትግርኛ ልዩነት አለው። ከዚህ ውጭ የብሔረሰብ ማንነትን በሚመለከት ከትግራይ ጋር በባሕል፣ በታሪክ፣ በመልክዓምድር፣ በሥነ ልቦናና በመሳሰሉት ዋና ዋና የማንነት መሥፈርቶች አንገናኝም።"

### ኢኮኖሚ፣ ሐገራዊ አስተዋጽዖ

"የወልቃይት አብዛኛው ሕዝብ በግብርና ሙያ የሚተዳደር ነው፤ የወባ በሽታን፣ አንበሳና ነብሩን፣ የጊንጥንና የእባብን ንክሻ ተቋቁሞ መዘጋ ወልቃይትንና ሑመራን የመሰሉ ገናና የእርሻ ቦታዎችን ያለማ ማኅበረሰብ ነው፤ በኢትዮጵያ ታዋቂ የነበረውን የሜካናይዝድ እርሻ በመጠቀም (በአንድ ወቅትም ከ1500 ያላነሱ ትራክተሮችን በመጠቀም) ሰሊጥ፣ ጥጥና ማሽላ በገፍ በማምረት አካባቢውን አለምቷል። በእነዚህ የሰሊጥና የጥጥ ልማት ዘመናትም ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ታላላቅ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቁም ነገሮችን አከናውኗል። ምንም እንኳ አካባቢው የመልማት ዕድል ባያገኝም የወልቃይት ሕዝብ በተለያዩ የሐገሪቱ ክልሎች ተሰድዶ ዘመናዊ እርሻን በማስተዋወቅ ላይ ያለ ሕዝብ ነው።"

እንደተወካዮቹና የሐገር ሽማግሌዎቹ ገለጻ፣ የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኛነት የማንነት ጥያቄ አሁን የተነሣ አይደለም፤ ሕወሓት በትጥቅ ትግል ላይ ሳለ አካባቢውን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተነሣና ከ1983ዓ.ም በኋላም በሕገ መንግሥቱ መሠረት ምላሽ ያልተሰጠው በየጊዜው እየተንከባለለ የመጣ ጥያቄ ነው።"

### ደረሱ የተባሉ ተጽዕኖዎችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

የወልቃይት ማኅበረሰብ አባላት፣ የሐገር ሽማግሌዎችና የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በመንደርደሪያው ላይ በተጠቀሰው ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ውስጥ፣ በአጠቃላይ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የሚከተሉት ተጽዕኖዎችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደደረሱ አመልክተዋል፡[2]

- ልጆቻቸው በቋንቋቸው እንዳይማሩና በግድ በትግርኛ እንዲማሩ መገደዳቸውን ገልጸዋል፣
- በየትኛውም የክልሉ መ/ቤት በትግርኛ የሥራ ቋንቋ በግድ እንዲናገሩ መደረጋቸውን አብራርተዋል፣
- የአማራን ባሕል ቀይራችሁ የትግራይን ባሕል በግድ ተቀበሉ መባላቸውን ገልጸዋል፣
- የአካባቢያው ጥንታዊ የሐገርና የአካባቢ ስሞች ማለትም የወረዳ፣ የከተማ፣ የመንደር፣ የወንዝና የምንጭ ፣ የጋራና የሸንተረር ስያሜዎች በትግርኛ ሥያሜ መለወጣቸውን ገልጸዋል፣

[2] ተወካዮቹ በደብዳቤአቸው የገለጹአቸውንና አንዳንድ ምስክሮችም ያስረዷቸውን አንዳንድ አቤቱታዎች ትክክለኛነት፣ ተጎጂዎቹን በቀጥታ በማግኘት ለማጣራት በአካባቢው ያለው የፖለቲካ፣ የጸጥታ፣ የባህል ተጽዕኖ እንዲሁም የሰመጉ የአቅም ውሱንነት አላስቻለም።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

- በትግራይ ባሉ መ/ቤቶች የወልቃይት ተወላጆች 5 ከመቶ፣ የትግራይ ተወላጆች ደግሞ 95 ከመቶ ሲሆኑ ያሉትም እኩል ዕድልና ሥልጣን እንደሌላቸው አመልክተዋል፣
- አንዳንድ የሕወሓት የአካባቢው ባለሥልጣናት የወልቃይት ተወላጅ ወንዶችን በማሠር ሚስቶቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን በግድ መድፈራቸውን ምስክሮች ገልጸዋል፣
- በማንኛውም መድረክ እንዳይናገሩ፣ ሰብዓዊ መብቶቻቸውን እንዳይጠቀሙ መደረጋቸውን፣ ከተናገሩ ደግሞ የድሮ ሥርዓት ደጋፊ ናቸው ወዘተ በማለት እንዲሳቀቁና እንዲታሠሩ መደረጋቸውን አስረድተዋል፣
- ትግራይ አይደለንም ወልቃይቴ ነን ያሉት በቀጥታ ሀብትና ንብረታቸውን መወረሳቸውን፣ መሬታቸው ተነጥቆ ለትግራይ ተወላጆች በመሰጠቱ የወልቃይት ተወላጆች ለድኅነት መዳረጋቸውን፣ በግልባጩም የተመረጡ የትግራይ ተወላጆች አላግባብ ሀብታም እንዲሆኑ መደረጉን ገልጸዋል፣
- ለዘመናት የወልቃይት ገበሬዎች ሲያርሱት የነበረ መሬት ተነጥቆ ለትግራይ የእርሻ ድርጅት መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡ መሬታቸውን የተቀሙ የወልቃይት ገበሬዎች ከአካባቢው እየተሰደዱ በአማራ ክልል በሶሮቃ፣ በአብርሃጅራ፣ በአብደራፊ፣ በመተማ፣ በቋራ፣ በሽሕዲ፣ በቤንሻንጉልና በጋምቤላ ክልሎች ተሰድደው የእንደሚገኙም ገልጸዋል፡፡ በሠፈራ የመጡና ከአካባቢው ባለሥልጣናት ጋር ልዩ የጥቅም ትስስር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች ግን ዛሬ ከሁለት ሔክታር አልፈው የአምሳና የመቶ ሔክታር ከዛም በላይ ባለቤቶች ሆነው እንደሚገኙ፤ በአጠቃላይ በአካባቢያቸው አልምተው እንዳይጠቀሙ አድሎ የተፈጸመባቸው መሆኑን አመልክተዋል፣
- እንደ ማሕበረሰቡ ተወካዮችና አባላት ገለጻ፣ ከመንገድ አንፃር የትግራይ አካባቢ ከወረዳ ቀበሌ የሚያገናኝ ጥርጊያ መንገድ በብዛት የተሠራ መሆኑን፣ የወልቃይት አካባቢ ግን ከወረዳ ቀበሌ ይቅርና ከወረዳ ወደ ወረዳ የሚያገናኝ እንኳ በቅጡ እንዳልተሠራ ገልጸዋል፡፡ ዛሬም ከወሊድ ጋር ተያያዥ በሆኑ የጤና ችግሮች የሚሰቃዩ የወልቃይት እናቶችና ሕፃናት  በርካታ መሆናቸውንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡
- ዛሬ ብዙ የትግራይ አካባቢዎች የንጹሕ ውኃ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፣ በወልቃይት ግን እንስሳና ሰው በአንድነት የሚጠጡበት ቦታ በብዛት ይገኛል፣ በቅርብ የመጡ የትግራይ ሠፋሪዎች ቧንቧ ውኃ ሲዘረጋላቸው ጥንታዊው የወልቃይት ማኅበረሰብ ግን ምንም ውኃና ጉድጓድ አላገኘም፡፡
- የሕክምና ተቋማትም በተመሳሳይ ለትግራይ ተወላጆች በሚጠቅም መልኩ የተሠሩ ናቸው፡፡ ከትምህርት ተቋማትም አንድም ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ በወልቃይት አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡
- በትግራይ ክልል ሥር መሆን አንፈልግም ብለው የተቃወሙ ከ300 በላይ የሚሆኑ የወልቃይት ተወላጆች ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተለያየ ጊዜ ከየቤታቸው በጨለማ ታፍነው ተወስደው መጥፋታቸውን ገልጸዋል፣

## የማሕበረሰቡ አቤቱታ

በማጠቃለያም የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኛነት የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በተለያዩ ቀናት ለሰመጉ በጽሁፍ ባቀረቧቸው ማመልከቻዎች፡

- ከዚህ በላይ ያነሷቸው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በሕጋዊ መንገድ ምላሽ እንዲያገኙ፣
- በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት መሠረታዊ መብቶቻቸው እየተጣሱባቸው በመሆኑ እየደረሰባቸው ያለው በደል በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲፈታ፣
- ከማሕበረሰባቸው አባላት ጋር መወያየት እንዲፈቀድላቸው፣
- የሕግ ከለላ እንዲሰጣቸው፣
- የሕዝብ ወኪሎች በራሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በሃብታቸው ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸውና የሕግ ከለላ እንዲደረግላቸው፣

"በታላቅ ትሕትና እንጠይቃለን›› ሲሉ ቅሬታና አቤቱታቸውን አሰምተዋል ፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ተጎጂዎቹ እንደሚገልጹት እየተሰጣቸው ያለው መልስ ‹‹መሬቱ ወደዳችሁም ጠላችሁም የትግራይ መሬት ነው፡፡ ለቅቃችሁ ወደ አማራ ክልል መሄድ ትችላላችሁ›› የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ የሚያነሡትንም ‹‹የደርግ ርዝራዥ፣ የሰማያዊ ፓርቲ፣ የግንቦት ሰባትና የሻዕቢያ ተላላኪዎች ናችሁ›› በማለት እንደሚያሸማቅቋቸው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖርና የአካል ደኅንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበርና የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸው በአንቀጽ 2(1) እና (2) ይደነግጋል፡፡ የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 ‹‹ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሠሥ በሕይወት የመኖር የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 2 በዘር፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌላ አስተያየት ወይም በኅብረተሰብ ምንጭ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ ዐቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም ሰው በመብቶቹና በነጻነቶቹ የመጠቀም መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 20 (1) ሁሉም ሕዝቦች የራሳቸውን የፖለቲካ ዐቋም ይወስናሉ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማታቸውን ራሳቸው በነጻነት በመረጡት ፖሊሲ መሠረት ያካሂዳሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

ኢትዮጵያም ይህን ቻርተር የተቀበለች ሐገር እንደ መሆኗ መጠን እነዚህን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39(1) እና (2) ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እንዲሁም ቋንቋና ባሕሉን የማዳበር፣ የማስፋፋት፣ ታሪኩን የመንከባከብ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

## 1.1 በምርመራው ሥራ የተሸፈኑ አካባቢዎች

የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኛነት የማንነት ጥያቄ ከማንሣቱ ጋር በተያያዘ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በተፈጸመባቸው አካባቢዎች ማለትም በወልቃይት፣ በጎንደር፣ በሶሮቃና በሌሎች አካባቢዎች የሰመጉ ባለሙያዎች በመገኘትና በመንቀሳቀስ ለመሥራት ችለዋል፡፡

## 1.2 የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በምርመራው ከተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮች መካከል ዋነኞቹ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ የዓይን ዕማኞችና ምስክሮች እንዲሁም የማኅበረሰቡ ተወካዮች ናቸው፡፡ የትግራይ ክልልና የምዕራባዊ ትግራይ ዞን አስተዳደርን እንዲሁም የወልቃይት ወረዳ አስተዳደርን ለማግኘት የተደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ለወደፊቱ በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ አግባብ ካላቸው የክልሉ መንግሥት መዋቅሮች ጋር ግንኙነት የማድረጉና መረጃ የመቀበሉ ጥረት ይቀጥላል፡፡ በተጨማሪም የሰመጉ ባለሙያዎች ወደ መስክ ምርመራ ከመሰማራታቸው በፊትና በኋላም ተዛማጅ ሠነዶችን ፈትሸዋል፡፡ ሰመጉ በዚህ ምርመራው ችግሩን በሥፍራው ተገኝቶ በመመልከትና የተለያዩ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ይህንን ሪፖርት አዘጋጅቷል፡፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

### 1.3 በምርመራ ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- በአጠቃላይ በሐገሪቱ ያለው ፖለቲካዊ ኹኔታ በውጥረት የተሞላ መሆኑና በተለይ በአሁኑ ወቅት እንደ ወልቃይት ባሉ ሥፍራዎች ገብቶ የምርመራ ሥራ ለማከናወን አስቸጋሪና አደገኛ መሆኑ፣ የመንግሥት የደኅንነትና የጸጥታ ኃይሎች ከፍተኛ ክትትል ማድረጋቸው፣
- ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ እስካሁን ሰመጉ ያለበት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የምርመራ ቁሳቁስ እጥረት፣ ሰመጉ በአሁኑ ወቅት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞባቸዋል በሚባሉ ቦታዎች ለመገኘትና እንደ አስፈላጊነቱ ተመላልሶ ተደጋጋሚ የምርመራ ሥራ ለማካሄድ ለባለሙያዎቹ የመጓጓዣ፣ የአበል ምግብና ማደሪያ ወጪ … ለመሸፈን እየተቸገረ መገኘቱ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡

ይሁንና ሰመጉ ከላይ የተጠቀሱትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በጠንካራ ሠራተኞቹና አባሎቹ የዓላማ ጽናትና ወጪዎችን በግልና በብድር በመሸፈን ጭምር በመቋቋም ምርመራውን ለማድረግና ይህንን ሪፖርት ለማዘጋጀት ችሏል፡፡

## 2. የማንነት ጥያቄ በማንሳት ምክንያት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የወልቃይት ተወላጆች የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ በማንሣታቸው በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የሰብዓዊ መብቶቻቸው ተጥሰውባቸዋል፡፡

### 2.1 ሕገ ወጥ ግድያ

የወልቃይት ነዋሪዎች፣ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦችና የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ለሰመጉ እንደገለጹት፣ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ገና በትጥቅ ትግል ላይ ከነበረበት ከ1983ዓ.ም በፊት ጀምሮ፣ የወልቃይት ተወላጆች በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ‹‹እኛ አማሮች እንጂ ትግሬዎች አይደለንም›› በማለት የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ ሲያነሱ ቆይተዋል፡፡ ተጎጂዎቹና የኮሚቴው አባላት እንደሚሉት፣ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም አካባቢው ወደ ትግራይ መካለሉን ሲቃወሙና የማንነት ጥያቄያቸውንም በሚያገኙት አጋጣሚ ሲያነሱ ቆይተዋል፡፡

ይህንና መሰል ተቃውሞ በሰላማዊ መንገድ ባሰሙ የስም ዝርዝራቸው ከዚህ በታች በተገለጸው የወልቃይት ማኅበረሰብ አባላት ላይ ሕገ ወጥ ግድያ መፈጸሙንም ሰመጉ ጽ/ቤት ድረስ መጥተውና የሰመጉ ባለሙያዎችም መስክ ድረስ ሄደው ያነጋገሯቸው የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፣ የተጎጂ ቤተሰቦችና የወልቃይት ነዋሪዎች ለሰመጉ አረጋግጠዋል፡፡ ግድያውንም የፈጸሙት በአካባቢው የሚገኙት የሕወሓት አመራሮችና ታጣቂዎች፣ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም የትግራይ ክልል መንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መሆናቸውንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ይበይን ተገኝ | ወፍ አርግፍ አድጋሰኝ | የማንነት ጥያቄ በማንሣቱ የተገደለ |
| 2 | ፈረደ ዘርዐይ | ኮሊታኖ ጣቢያ | ›› |
| 3 | ምሕረት ገብተው | ኮሊታኖ | ›› |
| 4 | አረፋይኔ መኮንን | ደንጎቻ | ›› |
| 5 | ቄስ በለጠ ተሰፋይ | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 6 | ገ/ማርያም ዘለቀ | ኮሊታ ጣቢያ | ›› |
| 7 | መርድ አፍተራሪ | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 8 | አለነ ቢራራ | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 9 | አዳነው ርስቱ | ›› | ›› |
| 10 | አዲሰይ ጠጁ | ›› | ›› |



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 11 | ተገኝ ነጋ | ኮሊ.ታይ ጣቢያ | ›› |
| 12 | ገ/መድኅን ዘርፉ | ብላንባ | ›› |
| 13 | ማማይ በላይ | አዲ.ጋባ | ›› |
| 14 | አርአያ መንግሥቱ | ከሊ.ታይ | ›› |
| 15 | እንዳልካቸው ጠጁ | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 16 | እያሱ አለነ | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 17 | ነጋ አስረሴ | አዲ.ጋባ | ›› |
| 18 | ግራዝማች ወልዴ | ›› | ›› |
| 19 | ተድላ ጥሩነህ | ቃፍቲያ ወረዳ | ›› |
| 20 | አጥናፌኝ ዓለማየሁ | ባላምባ ቀበሌ | ›› |
| 21 | ልጃለም ታዬ | ቦምቢ.ያ | ›› |
| 22 | ያለምእሸት | ቦምቢ.ያ | ›› |
| 23 | ደጀን ማሞ | ኮኮራ ማርያም | ›› |
| 24 | ባሕታ ደምሰው | ወፍ አርግፍ | ›› |
| 25 | አንጋው መንበር | ዳንሻ | በእሥር ላይ እንዳለ ሕይወቱ ያለፈ |
| 26 | ንጉሤ መንበር | ዳንሻ | ›› |
| 27 | ፈጠነ ገብሬ | ዳንሻ | ›› |
| 28 | መርድ ገ/ሚካኤል | ወልቃይት ኩሌታ | ›› |
| 29 | ገብሬ ገሹነህ | ›› | ›› |
| 30 | አታላይ ዓለም | ›› | ›› |
| 31 | ቀኛሽ ወልዴ | ›› | ›› |
| 32 | ግፋቸው ዳኜ | ›› | ›› |
| 33 | ንጉሤ የኒላ | ቃፍታ | ›› |
| 34 | ርስቱ ግርማይ ተስፋይ | ማይካድራ | ›› |

### 2.2. ታፍነው ተወስደው የደረሱበት የማይታወቅ፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17(1) ‹‹በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነጻነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡›› የሚለውንና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 9 ‹‹ሰው በዘፈቀደ ሊያዝ፣ ሊታሠር ወይም ሊጋዝ አይችልም›› ተብሎ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሱት ሰዎች ታፍነው ከተያዙበት ቀን ጀምሮ የት እና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ እስካሁን ድረስ የታወቀ ነገር የለም፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በሪ አዲሱ | 9 | ማለደ ነጋ | 17 | እያሁነይ ወንደቸዋል |
| 2 | ጆቴው ታምሬ | 10 | ጎሹ ኃይሌ | 18 | ደረጀ አንጋው |
| 3 | ሲሳይ ተስፋሁኔ | 11 | አለበል ኃይሌ | 19 | አለኸኝ ጸጋየሱስ |
| 4 | ባየው ቢያድግልኝ | 12 | ወጋህታይ ገ/ሥላሴ | 20 | ወንድም ኃይሌ |
| 5 | አታላይ ዘነበ | 13 | ሃፍቴ ዘነበ | 21 | እምየው አውሃራ |
| 6 | ሲሳይ ዘነበ | 14 | አዳነ ታደሰ | 22 | አስማማው በለጠ |
| 7 | ገ/መድኅን የኒላ | 15 | ማሙ ደስታ | 23 | ዐወቀ ትኩእ |
| 8 | ማሞ ዘውዴ | 16 | መሸሻ ሞላ | 24 | እንየው አውሃራ |

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | እንዳሻው ታፈረ | 48 | ሰረበ በየነ ቢተውልኝ | 71 | ደረጀ አንጋው |
| 26 | ዋኘው አባጣለው | 49 | ወልዴቂስ ያዕበየው | 72 | ወንድም ኃይሌ |
| 27 | ዓለም ባዬ | 50 | በየነ አየለኝ | 73 | ተካልኝ ተስፋየ |
| 28 | አያሌው ሰሙ | 51 | ገብረ ሥላሴ ረዳ | 74 | ተድላ ኃይሌ |
| 29 | አብርሃ ነጋ | 52 | ሀፍቱ ይርጋ | 75 | ለምለሙ ፈረደ |
| 30 | ጎይቶም ሃረሳ | 53 | ድራር ገሠሠ | 76 | ምሕረተይ አበበ |
| 31 | ሃብቱ ይርጋ | 54 | ሊላይ ሐድጉ | 77 | ንጋቱ ተርፋይ |
| 32 | ደስታ ልጃለም | 55 | ርስቀይ ኃይሌ | 78 | ተክላይ ልጃለም |
| 33 | ያዘዘው ላቀው | 56 | አሳመነ አታላይ | 79 | አበበ ተፈራ |
| 34 | ይግዛው ዘገየ | 57 | ተበጀ በቀለ | 80 | ዳምጤ ታከለ |
| 35 | ሙላው ካሣሁን | 58 | ሐየሎም ይርጋ | 81 | ተገኝ በላይ |
| 36 | ፀሐዬ ወልዴ | 59 | ገሬ ረዳ | 82 | እንየው ውብነህ |
| 37 | በርሄ ሐጎስ | 60 | አያሌው ሰሙ | 83 | ነጋ ተበጀ |
| 38 | አለባቸው መብራቱ | 61 | ፋንቱ ሲሳይ | 84 | ይርሳው ዘውዴ |
| 39 | ጎይትኦም ሃድጉ | 62 | ተካልኝ ተስፋየ | 85 | ተፈራ ሊላይ |
| 40 | ኃይሉ ልይነህ | 63 | ሐጎስ አታላይ | 86 | ጌጡ ጠለ |
| 41 | አለባቸው ደፈርሻ | 64 | አለሽኝ ጸጋየ | 87 | ወርቁ አይጠገብ |
| 42 | ገብርሔት ባሕታ | 65 | ተክሌ ልጃለም | 88 | ፈረደ ፀሐይ |
| 43 | ሽተይ አያልነህ | 66 | ፋንታሁን ገበየሁ | 89 | አለማየው ዘነበ |
| 44 | ማሌ ዘነበ | 67 | ፈረደ ዘርአይ | 90 | ተካልን ጸጋይ |
| 45 | ፋንቱ ተገኝ | 68 | እንኳየነ ለገሠ | 91 | አለቃ ባየ |
| 46 | ቻሉ ወርቅነህ | 69 | ዓለሙ ለገሠ | 92 | ልዑል መስፍን |
| 47 | ሰፊ ሲሳይ | 70 | ርጥበይ አጽብሃ | 93 | የሳው ዘውዱ |

**አቶ ሊላይ ብርሃኔ በየነ፡**

*ዕድሜው 39 በንግድ ሥራ የሚተዳደር ሲሆን፣ በወልቃይት የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ነው። በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የወልቃይትን ሕዝብ የማንነት ጥያቄ በማስተባበርና ለሚመለከታቸው የወረዳ፣ የክልልና የፌደራል መ/ቤቶች ከሌሎች የወልቃይት ተወላጆችና የኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን የሕዝቡን የማንነት ጥያቄ በማንሣት ይታወቃል። መጋቢት 9 ቀን 2008ዓ.ም ከቀኑ 8:00 አካባቢ ከጎንደር ወደ ሑመራ በመጓዝ ላይ እንዳለ ማይደሎ አካባቢ ሲደርስ በልዩ ኃይሎችና በደኅንነቶች ከተሣፈረበት የሕዝብ ማመላሻ መኪና ውስጥ በኃይል እንዲወርድ ተደርጎ ታፍኖ ተወስዷል። ይጓዝበት የነበረው መኪና ሹፌር፣ ትኬት ቆራጭና ረዳት፣ አቶ ሊላይ ታፍኖ መወሰዱን ለሕዝቡ በማጋለጻቸውና ፍርድ ቤት ቀርበው በመመስከራቸው ድብደባ ተፈጽሞባቸውና ለሁለት ወር ታስረው ተፈትተዋል።*

የወልቃይት ሕዝብም ‹‹አቶ ሊላይ ሕጋዊ ጥያቄ በመጠየቁ ታፍኖ ተወስዷል፤ ስለዚህ ያለበትን ቦታ በአስቸኳይ አሳውቁን ካጠፋም በግልጽ ፍርድ ቤት ይቅረብ›› በማለት በ11/07/2008ዓ.ም በዳንሻ ከተማ የተቃውሞ ሰልፍ ወጥቷል። አቶ ሊላይ ለረዥም ጊዜያት ታፍኖ ተወስዶ የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ቆይቶ በመጨረሻም ሕዝቡ ጥያቄውን ባለማቆሙ በ26/07/2008ዓ.ም ሑመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቧል። ቀጣይ ቀጠሮም ለሚያዝያ 12 ቀን 2008ዓ.ም ተሰጥቶ ነበር። የሑመራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቶ ሊላይን በነጻ ቢያሰናብታቸውምና እንዲፈቱ ቢወስንም ነገር ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ሰዓት አቶ ሊላይ በሑመራ ማረሚያ ቤት በእሥር ላይ ይገኛሉ።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

## 2.3. ድብደባና ማሠቃየት

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ‹‹ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ የሰዎች የአካል ደኅንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ደንግጓል፤ ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚከተሉት ግለሰቦች ድብደባና ማሠቃየት ተፈጽሞባቸዋል፡፡

1. **አቶ ልዑላይ ነጋ፡-** ዕድሜያቸው 40፣ የወልቃይት ወረዳ አድረመጥ ነዋሪ ናቸው፡፡ ነሐሴ 30ቀን 1997 ዓ.ም አድረመጥ ከተማ ሆቴል ውስጥ አርፈው በነበሩበት ወቅት የአድረመጽ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ‹‹ይህ ሆቴል ወልቃይቴ የሚገባበት አይደለም›› በማለት በሽጉጥ አፈሙዝ ከመቷቸው በኋላ በጥይትም ተኩሰው አፍንጫቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰውባቸዋል፤ አፍንጫቸው ተሰብሮአል፤ ከፍተኛና ተከታታይ ሕክምና ሲወሰዱ ቆይተዋል፡፡ የደበደባቸው የፖሊስ አዛዥ እስካሁን ድረስ በሕግ አልተጠየቀም፡፡

2. **አቶ ታደሰ ጎይቶም፡-** ዕድሜ 30፣ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ናቸው፡፡ የወልቃይትን ጥያቄ ትመራለህ በሚል መጋቢት 17 2007 ዓ.ም. በአዲ ጎሹ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ በሕገ ወጥ መንገድ ተይዘው ከመኖሪያ አካባቢያቸው በራቀው የአክሱም ከተማ እስር ቤት ታስረው ቆይተዋል፡፡ በእሥር ላይ በነበረቡት ወቅት መጋቢት 29 ቀን 2007ዓ.ም በእሥር ቤት ጠባቂዎች ከፍተኛ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ከአምስት ወራት እሥር በኋላ ነሐሴ 15 2007 ፍ/ቤት ነጻ ብሎ አሰናብቷቸዋል፡፡

3. **አቶ መብራቱ ታከለ፡-** ዕድሜ 48፣ ጥር 12 ቀን 2008ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 አካባቢ ቃፕቲያ ቀበሌ ሆቴል ውስጥ እንዳለ የቃፕቲያ ቀበሌ ባለሥልጣናት የሆኑት ሊቀመንበሩ በብርጭቆ አፍንጫቸው ላይ ስለመቷቸው የአፍንጫ ስብራት ደርሶባቸዋል፤ ምክትል ሊቀመንበሩ እና የሚሊሻ ኮማንደሩ ከፍተኛ ድብደባ ስለፈጸሙባቸው ጉዳት ደርሶባቸው በጎንደር ቸቸላ ሆስፒታል ህክምና ተከታትለዋል፤ በኋላም የወልቃይት የማንነት ጥያቄን ካላቆምህ የአጎትህን ልጅ እንዳጠፋነው ሁሉ አንተንም እናጠፋሃለን በማለት ዝተውባቸዋል፡፡

## 2.4 ሕገ ወጥ እሥራት

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17(1) ‹‹ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ውጭ ነጻነቱን አያጣም›› ሲል ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች ደግሞ በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት እንዳላቸው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13 (3) ደንግጓል፤ ይሁን እንጂ ይሄንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በመተላለፍ የሚከተሉት ሰዎች በሕገ ወጥ መንገድ ታሥረዋል፡፡

| ተ.ቁ | የታሣሪው ስም | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባየሁ ካሣይ | 15/06/08 | ሑመራ | |
| 2 | ጎይቶም አማረ | 19/06/08 | ሑመራ | |
| 3 | ጎይቶም ርስቀይ | 30/06/08 | ሑመራ | |
| 4 | ዓሊጋዝ አየለ | 12/07/08 | ሑመራ | |
| 8 | ሞላ ኃይሉ | 12/07/08 | ሑመራ | |
| 9 | አሻግረው ገዛኸኝ | 12/07/08 | ሑመራ | |
| 10 | ሰጠኝ አረሮ | 12/07/08 | ሑመራ | |
| 11 | ሰሎሞን ግዛቴ | 12/07/08 | ሑመራ | |
| 12 | ማማዬ ደሳለኝ | 12/07/08 | ሑመራ | |



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | የታሣሪው ስም | የታሠረበት ቀን | የታሠረበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 13 | ባሕታ ጠጁ | 20/07/08 | ሑመራ | |
| 14 | ታደሰ ኀይቶም | 27/07/07 | አክሱም | ለ6 ወራት ታሥሮ በፍርድ ቤት ነጻ ተብሎ የተለቀቀ |
| 15 | ልዑላይ ነጋ | 13/01/98 | አዲረመጽ | ለ2 ቀናት ታስሮ በፍርድ ቤት ነጻ ተብሎ የተለቀቀ |
| 16 | ንጉሤ ደምሰው | 30/12/99 | ጎንደር | ለ9 ወራት ታሥረው ፍርድ ቤት በነጻ ያሰናበታቸው |
| 17 | ባየው ካሰኝ | የካቲት 2008 | ዳንሻ | በታጣቂዎች ተወስደው አሁን ሑመራ ፖሊስ ጣቢያ በእሥር ላይ ይገኛሉ |

## 2.5 የእርሻ መሬት፣ መኖሪያ ቤትና ንብረት መንጠቅ

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 የንብረት መብትን በሚደነግገው ምዕራፍ ውስጥ ንዑሥ ቁጥር 1፣ ‹‹ማንኛውም የኢትዮጵ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/ መሆኗ ይከበርለታል/ይከበርላታል›› በማለት ደንግጓል። በተመሳሳይ ምዕራፍ ንዑሥ ቁጥር 4፣ ‹‹የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸውም ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው›› ሲል በግልጽ ይደነግጋል። ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረውና ሌሎችም በዚህ መግለጫ ውስጥ ያልተቀሱ የወልቃይት አርሶ አደሮች በተለያዩ ጊዜያት የእርሻ መሬታቸው፣ የእርሻ መኪኖቻቸው እንዲሁም በድካማቸው ያመረቱትን ምርት በሙሉና በከፊል በአካባቢው ባለሥልጣናት ተነጥቀዋል። ይህ ሕገ ወጥ ድርጊትም እስከአሁን ድረስ እንደቀጠለ የአካባቢው አርሶ አደሮችና የሕዝቡ የማንነት ጥያቂ አስተባባሪዎች ለሰመጉ አመልክተዋል።

1. **አቶ ካሣ ይርሳው፡** ዕድሜያቸው 50፣ ነዋሪነታቸው ሑመራ ቀበሌ 01 ውስጥ ሲሆን፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪና በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው። በቃፍታ ሑመራ ወረዳ፣ ራውያን ውስጥ የሚገኝ ለ55 ዓመት የተገበረበትና ከአባታቸው በውርስ ያገኙትን 700 ሔክታር የእርሻ መሬት ከልጅነት ጀምሮ እያለሙ ቆይተዋል። በ28/01/2003ዓ.ም ያለምንም ሕጋዊ ምክንያት ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ፣ ተለዋጭ ቦታ ወይም ካሣ ሳይሰጣቸው የእርሻ መሬታቸውን ተነጥቀዋል። ከብዙ ሙግትና ውጣ ውረድ በኋላ 100ሄክታር የተመለሰላቸው ሲሆን፣ ቀሪው 600 ሔክታር መሬታቸው እስካሁን ድረስ እንዳልተመለሰላቸውና የተሟላ ፍትሕ እንዳላገኙ ለሰመጉ አመልክተዋል። ይህም የመብት ጥሰት የተፈጸመባቸው ወልቃይቴ በመሆኔ ብቻ ነው በማለት ከነቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸውን አስረድተዋል።
2. **አቶ ይለፍ በየነ፡** ዕድሜ 28፣ ቃፕትያ ወረዳ ዲካ ጣቢያ ማይካድራ አካባቢ የሚገኘውን 250 ሔክታር የሚሆን የቤተሰባቸውን የእርሻ መሬት ከሕግ አግባብ ውጭ ተነጥቀው ለተወሰኑ የትግራይ ተወላጆች ተሰጥቶባቸዋል፤ ይህም ሲሆን ምንም ዓይነት ምክክር እንዳልተደረገና ተለዋጭ ቦታ ወይም ካሣም እንዳልተሰጣቸው ለሰመጉ አመልክቷል። እንዲሁም በ1984 ዓ.ም. የአባታቸው የአቶ በየነ ጥሩነህ እና የአቶ ተድላ ጥሩነህ ንብረት የሆኑ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ የቀንድ ከብቶች በሕወሐት ታጣቂዎች ተዘርፈው ወደ ትግራይ እንደተወሰደባቸው ለሰመጉ ገልጸዋል። የእርሻ መሬታቸውንም የተነጠቁበት ምክንያት ወልቃይቴ በመሆናቸውና የአማራ ማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ እንደሆነ አቶ ይለፍ ለሰመጉ ጨምረው ገልጸዋል። በዚሁ የማንነት ጥያቄ ምክንያት አቶ ተድላ ጥሩነህም በወቅቱ የሕወሐት ታጣቃዎች መገደላቸው በዚህ ሪፖርት ገጽ 7 በሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 19 ላይ ተመልክቷል።
3. **አቶ ርስቃይ አደመ፡** ዕድሜ 40፣ ባለትዳርና የ3 ልጆች አባት ሲሆኑ ነዋሪነታቸው ቃፍታ ወረዳ፣ ማይካድራ ቀበሌ ነው። ታኅሣሥ 2003ዓ.ም በማይካድራ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ 30 ሔክታር የሆነ የእርሻ ይዞታቸውን የሕወሓት ታጋይ በነበረ ሻምበል ያለ አግባብ ተነጥቀዋል። እንዲሁም 126 ኩንታል የማሽላ ምርት ተወስዶባቸዋል። ወልቃይቴ በመሆኔ ብቻ ከአካባቢዬም እንድሰደድ ተደርጌአለሁ፣

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

በዚህም ምክንያት ለስደት ተዳርጌ በከፍተኛ እንግልትና መጉላላት ውስጥ እገኛለሁ በማለት ለሰመጉ አመልክተዋል።

4. **አቶ ሲሳይ ዘነበ፡** *ነዋሪነታቸው ቃፐቲያ ሑመራ ሲሆን፣ 18 የሚሆኑ የቀንድ ከብቶችና የግል መሣሪያቸው ሐምሌ 11 1973 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት በ ታጣቂዎች ተወስዶባቸው እስከዛሬ ድረስ እንዳልተመለሰ ለሰመጉ በተሰጠ የምስክርነት ቃል ተገልጾአል። በተጨማሪም አቶ ሲሳይ በሕወሐት ታጣቂዎች ታፍነው ተወስደው እስከዛሬ የደረሱበት እንደማይታወቅ በዚህ ሪፖርት ገጽ 8 ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 6 ላይ ተመልክቷል።*

5. **አቶ በርለይ ተበጀ፡** *ዕድሜ 65፣ ነዋሪነታቸው ቃፍቲ አደር ባዕከር ውስጥ ሲሆን 30 ሔክታር የሚገመት የእርሻ መሬታቸውን የአካባቢው ባለሥልጣናት እንደነጠቋቸውና መሬታቸውንም ለማስመለስ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ ‹‹ለምን መሬቴ ይመለስ ትላለህ?›› በማለት ሰኔ ወር 2005ዓ.ም ለአራት ቀናት ታሥረው እንደተፈቱ ለሰመጉ አመልክተዋል።*

6. **አቶ አደም አሊ፡** *ዕድሜያቸው 66፣ የሑመራ ቀበሌ 01 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው። ሰፊ ሐብት የነበራቸው፣ በጠንካራ አርሶ አደርነትና የተቸገሩትን በመርዳት ሐገር የሚያውቃቸው ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት የእርሻ መሬታቸውን፣ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎቻቸውን የምርት ውጤቶቻቸውን በአካባቢው ባለሥልጣናት እንደተነጠቁ ገልጸዋል። የተለያዩ የእርሻ ምርቶቻቸውንም ወደ ገበያ ወስደው እንዳይሸጡ የተለያዩ ጫናዎች፣ በደሎችና አድሎዎች ሲፈጸሙባቸው እንደቆዩ፣ በዚህም ችግር ምክንያት ልጆቻቸው ሐገር ለቀቀው እንደተሰደዱና እንዲሁም "አማራ ነኝ የምትለውን ካላቆምክ እንገድልሃለን" በማለት በየጊዜው ዛቻና ማስፈራሪያ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝና በዚህም ምክንያት በከፍተኛ ሥጋት ላይ እንደሚገኙ ለሰመጉ አቤት ብለዋል።*

7. **አቶ ኑሩ ኢብራሒም፡** *ዕድሜያቸው 54፣ የ25 ቤተሰብ አስተዳዳሪና በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው። "የወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ በማንሣቴ ብቻ ወልቃይት ሑመራ ውስጥ የሚገኝ 100 ሔክታር የእርሻ መሬቴን ጥር 2000ዓ.ም ተነጥቄአለሁ። በተጨማሪም ትራክተርም በአካባቢው ባለሥልጣናት ተነጥቄአለሁ። የተነጠቅሁትም የእርሻ መሬቴን ከትግራይ ለመጡ ሰዎች ሸንሽነው አከፋፍለውታል። ከኅዳር 2008ዓ.ም ጀምሬ በጫና ሚስቴንና ልጆቼን ጥዬ ከአካባቢዬ ተሰድጄ በሚያውቁኝ ሰዎች ቤት ተጠግቼ፣ እየተረዳሁ ነው ያለሁት።" በማለት ለሰመጉ ገልጸዋል።*

8. **አቶ አሻግር ዘውዴ፡-** *ነዋሪነቱ ቃፍቲያ ሑመራ ሲሆን፣ በእርሻ ሥራ የሚተዳደር አርሶ አደር ነው። ወልቃይቴ በመሆኑ ብቻ የእርሻ ትራክተርና አንድ ጓንዴ መሣሪያ ከሕግ አግባብ ውጭ በአካባቢው ባለሥልጣናት መነጠቁን ለሰመጉ ገልጾአል።*

9. **አቶ ገብሬ ተገኝ፡-** በ2007ዓ.ም 50 ሔክታር የእርሻ መሬታቸውን ተቀምተው ከአክሱም ለመጣ የትግራይ ተወላጅ ለሆነ ሰው እንደተሰጠባቸው ለሰመጉ አቤቱታ ያቀረቡ ተጎጂዎች በምስክርነት ገልጸዋል።

10. **አቶ ቻላቸው ኃይሌ፡** *ዕድሜ 60፡ ነዋሪነታቸው መተማ ወረዳ፣ ሽኽዲ ከተማ የሆነ በህዳር 8 1982 ዓ.ም. 151 ከብቶችና 92 ፍየሎች በወቅቱ የአካባቢው ሕወሐት ሠራዊት ኃላፊ በነበረ፣ በኋላም ወደ ጎንደር አዘዞ ክፍለ ጦር በተዛወረ ባለሥልጣን ተወስደባቸዋል፤ ንብረታቸው እንዲመለስላቸው ከሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደርና ከመተማ ወረዳ ምክር ቤት ደብዳቤ ቢጻፍላቸውም እስካሁን ድረስ ተፈጻሚ ሳይሆንላቸው ቀርቷል።*[4]

11. **አቶ ተሰማ ረታ፡-** *ዕድሜ 68፣ የሑመራ ነዋሪና የማንነት ጥያቄ አስተባባሪው ኮሚቴ አባል ናቸው። የኮሚቴው አባል በመሆናቸው ምክንያት ብቻ ሰባ ሔክታር መሬት እያረሱ በግድ የ130 ሔክታር መሬት ግብር እንዲከፍሉ እንደተደረጉ፣ ያልተጠቀሙበትን የትርፍ ግብር 983ሺ.ህ ብር እንዲከፍሉ ያለአግባብ እንደተወሰነባቸው፤ ቅሬታ ቢያቀርቡም ሰሚ እንዳላገኙ ለሰመጉ ገልጸዋል፤ አቶ ተሰማ ለሕይወታቸው በመሥጋታቸው ከመኖሪያቸው ሸሽተው በስደት ላይ ይገኛሉ።*

---

[4] ሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን፣ በቁጥር ዳከ208/122/መ በቀን 05/08/1985 እና መተማ ወረዳ ምክር ቤት፣ በቁጥር መወም/770/85 በቀን 28/03/85 የተጻፉ ደብዳቤዎች።



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council *

## 2.6 መሣሪያቸውን የተነጠቁ አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች

ስማቸው ቀጥሎ የተዘረዘረው የወልቃይት ተወላጆች፣ የወልቃይትን የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ብቻ መሣሪያቸውን እንደተነጠቁ ባለጉዳዮቹና ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል።

1. አቶ ዓባይ ማማይ ------ አዲረመጥ 13/06/2008ዓ.ም
2. አቶ የብርሹም አደመ----- አዲረመጥ 24/05/2008ዓ.ም (ሆቴሉ ውስጥ አማርኛ በማስዘፈኑ)
3. አቶ መኩተ መብራቱ ----- ዳንሻ 22/06/2008ዓ.ም
4. አቶ ብርሃኑ ፈረደ----- ዳንሻ 22/06/2008ዓ.ም
5. አቶ አህመድ መሐመድ ኑር-----ዳንሻ 22/06/2008ዓ.ም
6. አቶ አነጋው ጥሩነህ----- ዳንሻ 22/06/2008ዓ.ም
7. አቶ ይርጋ አዛናው----- ዳንሻ 22/06/2008ዓ.ም
8. አቶ ጎረፈይ አስገዶም - - - ባእከር 11/05/2008ዓ.ም
9. አቶ ጸጋይ ውብ ነህ - - - - ቃፕቲያ ጥር 2008ዓ.ም

ሌሎችም ስማቸው እዚህ ያልተጠቀሱ ሰዎች ስብሰባ ተጠርተው የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ ደጋፊዎች ስለሆናችሁ "መሣሪያችሁ ለእናንተ አይገባም፣ አስረክቡ" ተብለው በግዴታ በጥርና በየካቲት ወር 2008ዓ.ም ማስረከባቸውን ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል።

## 2.7 የተፈናቀሉ ዜጎች

የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ምክንያት ጫና ደርሶባቸው ለሕይወታቸው በመሥጋት ከ12/07/2008ዓ.ም ጀምሮ ከወልቃይት ጠገዴ ወደተለያዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ዜጎች ስም ዝርዝር በከፊል እንደሚከተለው ቀርቧል። ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከፊሎቹ ተፈናቃዮች በተሰደዱበት ቦታ ሲገኙ ከፊሎቹ ደግሞ ችግሩን መቋቋም ባለመቻላቸው ምክንያት ወደ መኖሪያቸው ለመመለስ ተገድደዋል። ይህንንም የሰመጉ ባለሙያዎች ተፈናቃዮቹ በሚገኙበት ቦታ ተገኝተው አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ተፈናቃዮቹና የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በሥፍራው ለሰመጉ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል።

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንድመይ ጎይትያም | 16 | ሰፈፈ ካሜ | 31 | ዓንቸ ማማይ | 46 | ፍሬው አምሳሉ |
| 2 | ሙሉ አዱኛ | 17 | ባበይ ነጋ | 32 | ብርሃኔ ያእብዮ | 47 | አለቃ ጸጋየ ወርቁ |
| 3 | የኔሁን በሪሁን | 18 | ግደይ አሰፋ | 33 | የኔሁን ባየ | 48 | ይዘዘው ማለደ |
| 4 | ጥጋቡ በሪሁን | 19 | የኛው ልጅ እሸት | 34 | አምባቸው በሬ | 49 | ቻላቸው ጸሐየ |
| 5 | ሽሙየ | 20 | መኮነን ያዘዘው | 35 | ባህሬ በራ | 50 | ሰጠኝ ማማይ |
| 6 | አቶ ጀጃው በሪሁን | 21 | መላኩ ቸኮል | 36 | ወ/ሮ አሉ ማሞ | 51 | ጥጋቡ በሪሁን |
| 7 | አቶ ዳኘው ጫቅሉ | 22 | ካሣ ጥሩ | 37 | ሙላው ይስማው | 52 | መሪ በላይ |
| 8 | አቶ ካሣሁን እሸቴ | 23 | ባቡ ለገሠ | 38 | ወርቅነህ ብርሃኔ | 53 | ኃይሌ ይርጋ |
| 9 | አቶ እሸቴ አዲሱ | 24 | አለባ ተክሌ | 39 | ግዛቸው ብርሃኔ | 54 | መብራቱ አማረ |
| 10 | አቶ ሽባባው አስማረ | 25 | ጸጋየ አግደው | 40 | አለባ ብርሃኔ | 55 | መኮነን ደስታ |
| 11 | ወ/ሪት ጥላነሽ መብራቱ | 26 | ጸጋ ፈለቀ | 41 | ፈታለው ማሞ | 56 | የሽፋና አዘዘው |
| 12 | ማርከሻው አይነኩሉ | 27 | ጸጋየ ሃብቴ | 42 | ፈስሃ ደሞዝ | 57 | ኢሳያስ ማለደ |
| 13 | አባተ አዲሱ | 28 | ብርሃኑ ፈረደ | 43 | ይደግ አግዘው | 58 | ባየ ንጉሤ |
| 14 | አልኸኝ አቻምየለህ | 29 | ዳኘው ጸጋሁን | 44 | መኩተ መብራቱ | 59 | ልዑል ረዘመ |
| 15 | ሰረበ ሙሉ | 30 | ገብሬ አበበ | 45 | እሸቴ አዲሱ | 60 | ይለፍ በየነ |



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ተ.ቁ | ሙሉ ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 61 | ሰማቸው ዋኘው አዳነ | 81 | ታየ መሰለ | 101 | መስፍን ቃኘው | 121 | ሙሉብርሃን ንጉሜ |
| 62 | ሲሳይ ጥላሁን | 82 | ፈጠነ ገብርየ | 102 | ጸጋየ ወርቁ | 122 | ጸጋይ ውብነህ ወንዳጥር |
| 63 | ቄስ እንዳልየው ባየ | 83 | ጸጋሁን መለሰ | 103 | ዲ/ን መኩሪያ አዛናው | 123 | ዘውዱ ገ/እግዚአብሔር |
| 64 | ዮርዳኖስ መስፍን | 84 | አበባው ካሣሁን | 104 | ማማይ ፍቃዱ | 124 | መንግሥቱ እንዳለው |
| 65 | ማሩ ብርሃኔ | 85 | ጎሽ ጥሩነህ | 105 | መብራቱ ዓለሙ | 125 | ተስፋይ መውሻ ሐጎስ |
| 66 | ሲሳይ አየለ | 86 | ጉዐይ ንጉሥ | 106 | ደጀን ለምልሙ | 126 | አብርሃ መብራቱ |
| 67 | ግደይ አሰፋ | 87 | ቻሌ ገቢያው | 107 | ወ/ሮ ልዕልት ቸኮል | 127 | አደምሃ ጂአሊ |
| 68 | ፍስሃ ደስታ | 88 | እነነይ አብደርቃድር | 108 | እንደሻው አንጋው | 128 | መብራቱ ጌታሁን |
| 69 | ፍታለው ማማይ | 89 | መሠረት ደምለው | 109 | አንጋው ማሙ | 129 | ነጋ የኔሁን |
| 70 | ግዛቸው ብርሃኑ | 90 | ማሬ በላይ | 110 | ዐወቀ ዘነበ | 130 | አብርሃ መብራቱ |
| 71 | መከተ መብራቱ | 91 | ደሴ ዐይቸው | 111 | በሬ ወንድምአገኝ | 131 | መስፍን አስማረ |
| 72 | ኤፍሬም አምሳሉ | 92 | ይናገር ደሴ | 112 | ሞላ አበበ | 132 | ካሣኝ ለማ |
| 73 | ልጃለም ከበደ | 93 | አወቀ ዘነበ | 113 | ጠጁ ጎበዜ | 133 | ነጋ ባንተይሁን |
| 74 | ባሕታ ዋኘው | 94 | አቶ ሻምበል አበበ | 114 | ዐየነው አታላይ | 134 | ተሰማ ረታ ተከላ |
| 75 | ሙሉ መስፍን | 95 | ተመስገን በሪሁን | 115 | ጥጋበይ ባየው | 135 | ግደይ አሰማረ |
| 76 | ሽባባው ወልዴ | 96 | አቶ ሻምበል አታላይ | 116 | ማሞ አዳነ | 136 | ሽሀይ ገብርጨርቆስ |
| 77 | መንግሥቴ ፈንቴ | 97 | ሞላ መብራቱ | 117 | ጸጋየ ሲሳይ | 137 | ተስፋሁን ኃይሌ |
| 78 | አባተ አዲሱ | 98 | ጋሻው ጥላሁን | 118 | አላቸው ገብረጊዮርጊስ | | |
| 79 | ሥዩም በሪሁን | 99 | ብርሃኑ አዲሱ | 119 | ሲሳይ ዳኘው | | |
| 80 | አታላይ ታደገ | 100 | ሽበላው ማለደ | 120 | ሙሉ ንጉሜ | | |

## 2.8 የአካባቢና የቦታ ሥያሜ ለውጥ

የወልቃይት ማኅበረሰብ አባላት፣ የሐገር ሽማግሌዎችና የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ለሰመጉ እንደገለጹት፣ የወልቃይትን ሕዝብ የማንነትና የታሪክ ጥያቄ ለማጥፋት እየተደረጉ ካሉ ጥረቶች መካከል ነባር የአካባቢና የቦታ ስሞችን በአዲስ ሥያሜ መቀየር ተጠቃሽ ነው። ከእነዚህም ውስጥ ከዚህ በታች ጥቂቶቹ በንፅፅር ቀርበዋል።

| ተ.ቁ | የቀድሞ ሥያሜ | አዲስ መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1 | ክባቦ | ሕይወት |
| 2 | እምባጋላ | አህፎረም/ማይጨው |
| 3 | ወይናት | ደደቢት ለካቲት/ድቭዝን |
| 4 | ሹመሪ | ሰላም |
| 5 | ማይሌሌ | ኃይሎም |
| 6 | ሊላብ | ዓለም ገነት |
| 7 | ማክሰኞ ገበያ | ከተማ ንጉሥ |
| 8 | ኩርባ ሎሚ | ናይሎሚ |
| 9 | ዲሽቃ | ሰላም |
| 10 | ግይጥ | ማይወይኒ |
| 11 | መንሽል | ማይለሐም |
| 12 | ባናት | ሂይወት እርሻ መካናይዜሽን |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## **የመብት ጥሰቶቹ አጭር መግለጫ**

ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ገና በትጥቅ ትግል ላይ ከነበረበት ከ1983ዓ.ም በፊት ጀምሮ፣ የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኛነት ማንነት ጥያቄ ከማንሣቱ ጋር በተያያዘ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በዚህ መግለጫ በዝርዝር ቀርበዋል። *በዚህ ሪፖርት ከተገለጹትና* በአካባቢው ባለሥልጣናት በሕዝቡ ላይ ከተፈጸሙት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ***ሕገ-ወጥ ግድያ***፤ የአማራ ብሔርተኛነት የማንነት ጥያቄ ያነሡ 34 የወልቃይት ተወላጆች ግድያ ተፈጽሞባቸዋል፣
- ***ታፍኖ መወሰድ***፤ የማንነት ጥያቄ በማንሣታቸው ምክንያት ቁጥራቸው 93 የሆነ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ታፍነው ተወስደው እስካሁን ድረስ ያሉበት አይታወቅም፣
- **ድብደባና *ማሠቃየት***፤ የአካባቢው ባለሥልጣናት የማንነት ጥያቄ ባነሡ ዜጎች ላይ ድብደባና ማሠቃየት ፈጽመዋል፣
- **ሕገ ወጥ *እሥራት***፤ ከማንነት ጥያቄው ጋር በተያያዘ 17 ሰዎች ሕገ-ወጥ እሥራት ተፈጽሞባቸዋል፣
- **የእርሻ *መሬት*፣ *መኖሪያ* ቤትና ንብረት *መንጠቅ***፤ የወልቃይት አርሶ አደሮች በተለያዩ ጊዜያት የእርሻ መሬታቸው፣ የእርሻ መኪኖቻቸው እንዲሁም በድካማቸው ያመረቱትን ምርት በሙሉና በከፊል በአካባቢው ባለሥልጣናት ተነጥቀዋል፣
- ***መኖሪያ መንጠቅ***፤ የወልቃይትን የአማራ ብሔርተኛነት የማንነት ጥያቄ ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ብቻ አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች መኖሪያቸውን ተነጥቀዋል፣
- **ከ*መኖሪያ መፈናቀል***፤ የወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኛነት ማንነት ጥያቄ በማንሣቱ ምክንያት የአካባቢው ባለሥልጣናት የሚፈጽሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በመሸሽ ዜጎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው ለስደት ተዳርገዋል፣
- **አድልዎና አስተዳደራዊ በደል**፤ ከቋንቋ፣ ከባህል፣ ከኢኮኖሚ፣ ከፍትሕ አሰጣጥና ከአስተዳደር ጋር በተያያዘ አድልዎና በደል ተፈጽሞባቸዋል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## ለ. የቅማንት ሕዝብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ መብት ጥሰት

### 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀፅ 3 እያንዳንዱ ሰው በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀስ 6(1) እና 9(1) ይህንኑ መብት አረጋግጦ መንግስታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በአንቀፅ 2(1)(2) ይደነግጋል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 14 ላይ ‹‹ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነትና ነፃነት›› እንዳለው በግልፅ ይደነግጋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በዚህ 141ኛ ልዩ መግለጫው፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚኖሩ የቅማንት ብሄረሰብ አባላት ያነሱትን የማንነት ጥያቄ ተከትሎ በተከሰተ ግጭት የደረሰውን የህይወት መጥፋት፣ የአካል መጉደል፣ ህገወጥ እስራት፣ የንብረት ውድመትና የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶችን በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

### 2. በምርመራ ሥራው ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

በአማራ ክልል በተለይም የማንነት ጥያቄው በተነሳባቸው አካባቢዎች ያለው ፖለቲካዊ ሁኔታ በውጥረት የተሞላ መሆኑ፣ በተለይ በአሁኑ ወቅት የቅማንት ማሕበረሰብ በሚኖርባቸው ሥፍራዎችና በተጎራባች አካባቢዎች እንደልብ ተዘዋውሮ የምርመራ ሥራ ለማከናወን አስቸጋሪና አደገኛ መሆኑ፣ የመንግሥት የደኅንነትና የጸጥታ ኃይሎች እንዲሁም ችግሩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አስተዳደር አካላት ከፍተኛ ክትትል ማድረጋቸውና ተጎጂዎችና ምስክሮችም በከፍተኛ ፍርትና ሥጋት ውስጥ በመገኘታቸው የተነሳ በቂ መረጃና ማስረጃ ለማሰባሰብ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ የቅማንት ማሕበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሱት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በሰመጉም ሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች ገለልተኛ አካላት ጊዜ ተወስዶ በበቂ ሁኔታ እንዲጠና ሰመጉ ከወዲሁ ያሳስባል፡፡

የቅማንት ማሕበረሰብ የብሔረሰብ ማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና ሌሎችም ምስክሮች ለሰመጉችበተጻፈ ደብዳቤና አቤቱታ እንደገለጹት፣ የቅማንት ማሕበረሰብ የብሔረሰብ ማንነት ጥያቄ ለአማራ ክልል መንግሥትና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሳያገኝ ዘግይቶ ቆይቷል፡፡ የአማራ ክልል ምክር ቤት በ2005 የሰጠውን ውሳኔ ባለማቀበል የቅማንት ማሕበረሰብ ተወካዮች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 13 2006 ዓ.ም. አቀረቡ፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ሳይገኝ በህዳር 25 2007 ዓ.ም. የአማራ ክልል ምክር ቤት የራሱን የውሳኔ ሀሳብ ይፋ አደረገ፡፡ በዚህም ውሳኔው በ8 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙ የ126 ቀበሌዎች የማንነት ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም፣ በ2 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙ 42 ቀበሌዎች ብቻ "የቅማንት ማሕበረሰብ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር" የሚል ውሳኔ በመጋቢት 02 2007 ዓ.ም. ወሰነ፡

ይህንን የአማራ ክልል ምክር ቤት ውሳኔ በመቃወም የማሕበረሰቡ አባላት ቅሬታቸውን በተለያየ ጊዜ ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡ የቅማንት ተወላጆች በአይከል ከተማ ላይ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ለሚመለከተው ክፍል ካስፈቀዱ በኋላ ሰኔ 7 ቀን 2007 ዓ.ም. የሰልፍ ጥሪ በሚተላለፍበት ወቅት ጥሪውን እንዲያስተላልፉ የተመደቡ ወጣቶች ጥሪ ማድረጋቸውን እንዲያቆሙ በክልሉ ልዩ ኃይልና ፖሊስ አባላት ይጠየቃሉ፡፡ ይህንን ተከትሎ በተፈጠረ አለመግባባት የክልሉ ልዩ ኃይልና የፖሊስ አባላት 6 ሰዎች በሕገ ወጥ መንገድ ተኩሰው መግደላቸውንና 7 ሰዎችን ማቁሰላቸውን ተወካዮችና ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ሕዳር 29 ቀን 2008 ዓ.ም. ገንዳ ውሃ ወረዳ ሽንፋ ቀበሌ ላይ በውስጣቸው የታጠቁ ሰዎች የሚገኙባቸው ሰዎች ሰልፍ ወጥተው "ሕገመንግሥቱ ይሻሻል"፣ "አንቀጽ 39 ይሰረዝ"፣ "የአማራ ክልል የሰጠውን ውሳኔ እንቀበላለን"፣ "የፌዴሬሽን ምክር ቤት (ፌዴራል መንግሥት የሰጠውን ውሳኔ እንቃወማለን" የመሳሰሉ መፈክሮችን ሲያሰሙ ውለዋል። ይህንኑ ተከትሎ መተማ ወረዳ ሽንፋ ቀበሌ የቅማንት ማሕበረሰብ አባላት ንብረት የሆኑ በርካታ ቤቶች እንደተቃጠሉ ምስክሮቹ ገልጸዋል። ከህዳር 29 ቀን ጀምሮ እስከ ታሕሳስ 4 ቀን 2008 ድረስ በተካሄደ ግጭት፣ የተኩስ ልውውጥና ጥቃት በተለያዩ ቀበሌዎች በርካታ ቤት፣ ከፍተኛ ንብረት፣ የእህል ክምርና እህል መቃጠሉን የቅማንት ማሕበረሰብ የብሔረሰብ ማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና ምስክሮች ለሰመጉ ገልጸዋል።

## 3. ሕገወጥ ግድያ፡

የማንነት ጥያቄው አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና ምስክሮች ለሰመጉ እንደገለጹት፣ የቅማንት ማሕበረሰብን የብሄረሰብ ማንነት ጥያቄ ተከትሎ የአማራ ክልል የጸጥታ ኃይሎችና ታጣቂዎች ጥቅምት 22 2008 ዓ.ም. ላይ-አርማጭሆ ወረዳ፣ ማውራ ቀበሌ ውስጥ በወሰዱት የኃይል እርምጃ በህገወጥ መንገድ የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ቀርቧል::

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ቀበሌ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ደስታው ጫቅሌ ዱባለ | ወ | 40 | ጫንቂያ | መምህር |
| 2 | አቶ ማንዴ ማሬ አራጌ | ወ | 32 | ምድራር | 9ኛ ክፍል ተማሪ |
| 3 | አቶ እንዳልክ እሸቴ ወንዴ | ወ | 25 | ምድራር | 8ኛ ክፍል ተማሪ |
| 4 | አቶ ደርሶ ጫኔ ተገን | ወ | 30 | ጫንቂያ | አርሶ አደር |
| 5 | አቶ አይጠገብ አዳነ መኩሪያ | ወ | 20 | ጫንቂያ | 12ኛ ክፍል ተማሪ |
| 6 | አቶ ታገለ ጉበና ሻረው | ወ | 56 | ወይኖች | አርሶ አደር |
| 7 | ጌታሁን ጸሀይ ወ/ኪዳን | ወ | 44 | ወይኖች | አርሶ አደር |
| 8 | አማረ ሰርፀ ከበደ | ወ | 43 | ወይኖች | አርሶ አደር |
| 9 | ጌታቸው ም ሬ ከበደ | ወ | 17 | ወይኖች | 1ክፍል ተማሪ |
| 10 | አለበል አንጋጄ ላቀው | ወ | 42 | ተክል ድንጋይ | አናፂ |
| 11 | ሞላ ይግዛው ንጉሴ | ወ | 70 | ብርላሆ | አርሶ አደር |
| 12 | ምህረቱ ተሸ ፍላቴ | ወ | 35 | ማውራ | አርሶ አደር |
| 13 | ጣሹ ዘመነ አለባቸው | ወ | 47 | ማውራ | አድሶ አደር |
| 14 | አበበ (ቴዲ) ደረሰ አያሌው | ወ | 15 | ማውራ | ተማሪ |
| 15 | ይስማው መካሻው ተገኑ | ወ | 57 | ማውራ | አርሶ አደር |
| 16 | አያልነሽ ማሬ አያሌው | ሴ | 13 | ማውራ | ተማሪ |
| 17 | ምህረት ታከለ አስፋው | ወ | 52 | ማውራ | ዘበኛ |
| 18 | ወ/ሮ እንይሽ አብተው ጠይማ | ሴ | 47 | ማውራ | የቤት እመቤት |
| 19 | መኩ ደርሶ ተስፋዬ | ወ | 28 | ጎንደሮች ማርያም | ተማሪ |
| 20 | አለፈ ማኔ አብተው | ወ | 16 | ጎንደሮች ማርያም | ተማሪ |
| 21 | ጮማየ ደምሴ ጣሰው | ወ | 38 | ጎንደሮች ማርያም | አርሶ አደር |
| 22 | ጠጁ ደምሴ ጣሰው | ወ | 38 | ጎንደሮች ማርያም | አርሶ አደር |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 4. በግጭቱ ወቅት የቆሰሉ ሰዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የቁስለኛው ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | ቀበሌ | ስራ | የደረሰበት ጉዳት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ገበይ ሰጡ ቸኮል | ወ | - | ማውራ | አርሶ አደር | እጃቸው ላይ የተጎዱ |
| 2 | አቶ ፈረደ አባተ | ወ | - | ጭላ ደወል | አርሶ አደር | እጃቸው ላይ የተጎዱ |
| 3 | አቶ አዲሴ ንጉሴ ተካ | ወ | | ማውራ | አርሶ አደር | ሆዳቸው ላይ የተጎዱ |
| 4 | አቶ ማሬ አያሌው | ወ | - | ማውራ | አርሶ አደር | እጃቸው ላይ የተጎዱ |
| 5 | አቶ ደሴ ደምሴ ጣሰው | ወ | - | ጎንደሮች ማሪያም | አርሶ አደር | - |
| 6 | አቶ ቀናው ብርሀኑ ድንቁ | ወ | 40 | ጫንቂያ | አርሶ አደር | እግርና እጃቸው ላይ የተጎዱ |
| 7 | አቶ አልቃድር ብዙነህ | ወ | 60 | ወይኖች | አርሶ አደር | እጃቸው ላይ የተጎዱ |
| 8 | አቶ ማለደ አስማረ አለነ | ወ | 60 | ባርላሆ | አርሶ አደር | ጭናቸው ላይ የተጎዱ |
| 9 | አቶ ገበየሁ ጥሩነህ ዘሌ | ወ | 45 | ምድራሮ | አርሶ አደር | እግራቸውን የተጎዱ |
| 10 | አቶ ልንገረው አንዳርጌ ተፈራ | ወ | 28 | ባርላሆ | አርሶ አደር | እጃቸው ላይ የተጎዱ |

ከዚህ በታች የሚታየው የሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋቶች መጠን በአስተባባሪ ኮሚቴው አባላት የቀረበ ነው

የተገደለ ሰው ድምር 74

የቆሰለ ሰው ድምር 39

አድራሻቸው የጠፋ ሰዎች 36

## 5. የደረሰ የንብረት ውድመት

የቅማንት ማሕበረሰብ የብሔረሰብ ማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና ሌሎችም ምስክሮች ለሰመጉ እንደገለጹት፣ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች በቅማንት ህዝብ ላይ የደረሰው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ከፍተኛ ነው፡፡ በርካታ መኖሪያ ቤቶችና ንብረት ተቃጥለዋል፣ የእህል ክምር ሙሉ በሙሉ ወድሟል፣ ከብቶቻቸው ተገድለዋል፤ ተዘርፈዋል እንዲሁም በርካታ ሰዎች ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለዋል፡፡

አስተባባሪ ኮሚቴዎቹ በጽሁፍ ለሰመጉ ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ጠቅላላ የወደመ ንብረት በገንዘብ ሲተመን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ቋራ ወረዳ ------------------------ 6,234,122 ብር
- መተማ ወረዳ --------------------- 81,667,294 ብር
- ጭልጋ ወረዳ -------------------- 58,816,760 ብር
- ታች አርማጭሆ፣ ማላ ኪዳነ ምህረት 1,744,000 ብር

**አጠቃላይ ድምር 148,462,176** ብር

ይህ ሪፖርት በመጠናቀር ላይ ባለበት ወቅት የቅማንት ብሄረሰብ የማንነት ጥያቄ አቅራቢ ተወካዮች ለሰመጉ እንዳመለከቱት በ12/07/2008 ዓ.ም. በላይ አርማጭሆ ትክል ድንጋይ ከተማ ውስጥ የቅማንት ብሄረሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል የሆኑት፡

1. አቶ ፀጋየ ምትኩ
2. አቶ ደጉ ገነት
3. ወጣት ክንዱ አሰፋ
4. አቶ ማዘንጊያ ላቀው

ከሥራ እየወጡ በነበሩበት ሰዓት ከ 3 (ሶስት) ተጨማሪ የቅማንት ብሄረሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ጋር ከፍተኛ ድብደባ እና የግድያ ሙከራ ተደርጎባቸዋል፡፡ እንዲሁም በ16/07/2008 ዓ.ም. ከምሽቱ 5:00 ጀምሮ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

በክልሉ ልዩ ሀይል አማካኝነት ከፍተኛ ተኩስ ተከፍቶና ቦንብ ተጥሎ ስማቸው ቀጥሎ የተገለጸው ሁለት ዜጎች ተገድለዋል።

1ኛ. ወ/ሮ ታድላ አዳነ እና
2ኛ. አቶ ሳሌ ተስፋሁነኝ

**ማሳሰቢያ**

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ወደፊት ጉዳት በደረሰባቸው የቅማንት አካባቢዎች በመገኘት የደረሱትን ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋቶች በጥልቀት ጥናትና ማጣራት በማድረግ መግለጫ ለማውጣት የተቻለውን ጥረት ያደርጋል። በዚህም ጥናት ከየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ማንነት፣ ብዛትና ምክንያት እንዲሁም ከየትኛውም አቅጣጫ ቢሆኑ የጉዳት አድራሾቹ ማንነት፣ ጉዳት ያደረሱበት ምክንያትና ሁኔታ ታውቆ ለሰብዓዊ መብት ቀውሱ አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጥ፣ የማያዳግም አዎንታዊና ትምህርት ሰጪ እርምጃ እንዲወሰድ ሰመጉ አበክሮ ያሳስባል። ይልቁንም የማሕበረሰቦቹን የማንነት ጥያቄ በሕግና በዴሞክራሲያዊ አግባብ ለመመለስ ከመጣር ይልቅ ጥያቄዎቹን ተንተርሶ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨትና ከሰብዓዊ መብቶች ቀውሱ የፖለቲካ ጥቅምና ትርፍ ለማግኘት የሚደረጉ የየትኛውም ወገን ድርጊቶች በሐገር፣ በሕዝብና በትውልድ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያመጡ ታውቆ ማንኛውም ወገን ከአፍራሽ ድርጊቶች እንዲቆጠብ ሰመጉ ይጠይቃል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

## ሐ. የቁጫ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ መብት ጥሰት

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 2 በዘር፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌላ አስተያየት ወይም በኅብረተሰብ ምንጭ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ ዐቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም ሰው በመብቶቹና በነጻነቶቹ የመጠቀም መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 20 (1) ሁሉም ሕዝቦች የራሳቸውን የፖለቲካ ዐቋም ይወስናሉ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማታቸውን ራሳቸው በነጻነት በመረጡት ፖሊሲ መሠረት ያካሂዳሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

ኢትዮጵያም ይህን ቻርተር የተቀበለች ሐገር እንደ መሆኗ መጠን እነዚህን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39(1) እና (2) ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እንዲሁም ቋንቋና ባሕሉን የማዳበር፣ የማስፋፋት፣ ታሪኩን የመንከባከብ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በዚህ 141ኛ ልዩ መግለጫው፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ በጋሞጎፋ ዞን የሚኖሩ የቁጫ ማሕበረሰብ አባላት ያነሱትን የማንነት ጥያቄ ተከትሎ የደረሱትን ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አስመልክቶ ሰመጉ 128ኛና 129ኛ ልዩ መግለጫዎች በ2005 ዓ.ም. ማውጣቱ ይታወሳል፡፡

የቁጫ ህዝብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ተወካዮች ለሰመጉ በመጋቢት 29 2008 ዓ.ም. ባቀረቡት የጽሁፍ አቤቱታ እንደገለጹት፣ ከሰመጉ መግለጫዎችም በኋላ የቁጫ ሕዝብን የማንነት ጥያቄ አቅርባችኋል ተብለው 42 የማኅበረሰቡ አባላት ታሥረው የዋስትና መብትም ተነፍገው ይህ መግለጫ ይፋ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ፍርድ ሳያገኙ ዐርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት በእሥር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ካሁን በፊት የተገደሉ ሰዎች ገዳዮቻቸው ለሕግ አልቀረቡም፡፡ ከ100 በላይ ዜጎችን በጥይት ያቆሰሉ ለሕግ አልቀረቡም፣ ተጎጂዎቹም ካሣ አላገኙም፡፡ የቁጫ ሕዝግ የማንነት ጥያቄ አንሥታችኋል ተብለው ብዛት ያላቸው የቁጫ ማኅበረሰብ አባላት ከመንግሥት ሥራ ተባርረዋል፣ ከእርሻቸው ተፈናቅለዋል፣ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይገኙ ተደርገዋል፣ ነጋዴዎች እንዳይነግዱ ተከልክለዋል፡፡ የማኅበረሰቡ የማንነት ጥያቄ አሁንም ድረስ ምላሽ ባለማግኘቱ ተወካዮቹ ለኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት ተደጋጋሚ አቤቱታዎችን እንዳቀረቡ ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የፌዴሬሽን ም/ቤት ለደቡብ ክልል ደብዳቤ እንደጻፈና ከክልሉ መልስ ጠብቁ እንደተባሉ፣ ለክልሉ የተጻፈው ደብዳቤ ግልባጭ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም እንደማይሰጣቸው እንደተገለጸላቸው የማኅበረሰቡ ተወካዮች ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸመባቸው ዜጎች ተገቢውን ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ ጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁ፣ ከሕግ አግባብ ውጭ ከሥራ የተባረሩት እንዲመለሱና የታሠሩትም እንዲፈቱ እንዲሁም የቁጫ ሕዝብ የማንነት ጥያቄም በሕገመንግሥቱና በዴሞክራሲያዊ አግባብ እንዲፈታ ሰመጉ መንግሥትን አበክሮ ይጠይቃል፡፡

## መ. የኮንቶማ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሰ የሰብዓዊ መብት ጥሰት

በተመሣሣይ መልኩ በደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን በማረቆ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የኮንቶማ ማሕበረሰብ አባላት የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ለሕገ ወጥ ግድያ፣ ለእሥራትና ንብረት ማውደም መዳረጋቸውን በማውገዝና መፍትሔ እንዲሰጥ ሰመጉ ባወጣቸው 33ኛ እና 35ኛ መደበኛ መግለጫዎች ውስጥ እንዲሁም በ114ኛ ልዩ መግለጫው በተከታታይ መጠየቁ ይታወሳል፡፡ ችግሩ እስካሁን ዕልባት አልተሰጠውም፡፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

የማኅበረሰቡ ተወካዮች አዲስ አበባ የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ም/ቤት በመመላለስ እስካሁን ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ለሰመጉ ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸመባቸው ዜጎች ተገቢውን ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ ጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁ፣ እንዲሁም የኮንቶማ ሕዝብ የማንነት ጥያቄም በሕገመንግሥቱና በዴሞክራሲያዊ አግባብ እንዲፈታ ሰመጉ መንግሥትን አበክሮ ይጠይቃል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በዚህ 141ኛ ልዩ መግለጫው፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚኖሩ የኮንቶማ ማሕበረሰብ አባላት ያነሱትን የማንነት ጥያቄ ተከትሎ በተከሰተ ግጭት የደረሰውን የህይወት መጥፋት፣ የአካል መጉደል፣ ህገወጥ እስራት፣ የንብረት ውድመትና የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶችን በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

## ማጠቃለያ

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑሥ አንቀጽ 3 ‹‹ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሠፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን በሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡›› ሲል ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ይህን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የማንነት ጥያቄዎች ጥልቅና ሰፊ በሆነ ጥናት ላይ ተመርኩዞ፣ በሕግ አግባብና በዴሞክራሲያዊ መንገድ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚደረግ ምክክርና ውይይት በአፋጣኝና በማያዳግም መልኩ ሊስተናገዱ ይገባል፡፡

መንግሥትም ለሕዝብ ጥያቄዎች የኃይል ምላሽ በመስጠት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ከመጣስ ይልቅ ሕገ መንግሥቱን፣ የአፍሪካን የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተርና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችን በማክበር የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስብርና ለመብቶች መከበር አስፈላጊውን ሁኔታ እንዲያሟላ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

## ማሳሰቢያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 15 ‹‹ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፤ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በቀር ሕይወቱን አያጣም›› ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ፡-

- የወልቃይት፣ የቅማንት፣ የቁጫና የኮንቶማ ማሕበረሰቦች ላቀረቡት የማንነት ጥያቄ በመንግሥት የተሰጠው የኃይል ምላሽ በምንም መልኩና በማንኛውም መለኪያ በሰመጉ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣
- የወልቃይት፣ የቅማንት፣ የቁጫና የኮንቶማ ማሕበረሰቦች የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ምክንያት ብቻ ሕይወት ያጠፉና እንዲጠፋ ትዕዛዝ የሰጡ፣ አፍና መሰወር፣ ሕገ ወጥ እሥርና የንበረት ነጠቃ የፈጸሙና ትዕዛዝ ያስተላለፉ የመንግሥት ኃላፊዎች በአስቸኳይ ለሕግ እንዲቀርቡ፣
- የወልቃይት፣ የቅማንት፣ የቁጫና የኮንቶማ ማሕበረሰቦችን የማንነት ጥያቄ በመጠየቃቸው ተፈናቅለው በተለያዩ አካባቢዎች በስደት የሚገኙ ዋስትና ተሰጥቷቸው በሰላም ወደሚኖሩበት አካባቢ እንዲመለሱና እንዲቋቋሙ እንዲደረግ፣

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

* ከሕግ አግባብ ውጭ የተነጠቁትን የእርሻ መሬት፣ የእርሻ መሣሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ንብረቶቻቸው በአስቸኳይ እንዲመለሱላቸው፣
* ግድያ ለተፈጸመባቸው ግለሰቦች ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ በአስቸኳይ እንዲከፈል፣
* ታፍነው ተወስደው ለረዥም ጊዜ የደረሱበት የማይታወቅ ሰዎች በሕይወት ካሉ የሚገኙበት ሥፍራ ለቤተሰቦቻቸው ተገልጾ እንዲጠየቁ፣ በሕይወት ከሌሉም ይህንን ድርጊት የፈጸሙና ትዕዛዝ ያስተላለፉ ኃላፊዎች በአስቸኳይ ለሕግ እንዲቀርቡና ካሣም እንዲከፈል፣
* በወልቃይት፣ በቅማንት፣ በቁጫና በኮንቶማ ማሕበረሰቦች የቀረበው የማንነት ጥያቄ የመብት ጥያቄ በመሆኑ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በፌዴራል ባለሥልጣናት በማሕበረሰቦቹ ላይ እየተፈጸመ ያለው አፈና፣ እሥር፣ ማሠቃየትና ንብረት ነጠቃ በአስቸኳይ እንዲቆም፣
* በኤፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የማንነት ጥያቄ ለሚያነሱ ማህበረሰቦች የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ፣ ተአማኒነት ያለውና ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ በወቅቱና በአፋጣኝ እንዲሰጥ ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና በመደወል ጥያቄ እንድታቀርቡ፤ ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት**
  ፖ.ሳ.ቁጥር :- 80001፣ ኢ.-ሜል:- national.parliament@ethionet.et፣
  ፋክስ :- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር :- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር :- 20122/1000፣ ኢ.-ሜል :- kumashih@gmail.com
  ፋክስ :- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር :- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 23698፣ ፋክስ :- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:-1031፣ ፋክስ:- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራልና አርብቶ አደሮች ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 5608፣ ኢ.-ሜል:- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ:-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር:-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
* **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር**
  ፖ.ሳ.ቁጥር:- 1370፣ ኢ.-ሜል: justabr@ethionet.et፣
  ፋክስ:- (+251) 011 551-7775፣
  የስልክ ቁጥር:- (+251) 011 551-3620፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ.-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ.-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ
- **ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ
- **ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ.-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ
- **ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ
- **ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council *

ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ * Human Rights Council

ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፣
የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት አባል እና
የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን ኮረስፖንዲንግ አባልም ነው፡፡